## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ታህሳስ 4 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**በመለስ ቢሮ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ለሁለት ቀናት 45 ከፍተኛ ባለስልጣናት ብቻ ዝግ ስብሰባ አደረጉ፤ የጅቡቲ የወደብ ታሪፍ ጭማሪ ተግባራዊ መሆን ጀመረ ፣ የነመለስ ልምምጥ እና የሰጡት እጅ መንሻ ገደል ገባ፤ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከፍተኛ መኮንኖች በገንዘብ ምዝበራ እርስ በርስ ተወነጃጀሉ፤ ከ7 ሚሊዮን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ተመዝብሮዋል፤ በርካታ የቃሊቲ እስር ቤት ፖሊሶች ስራቸውን እየለቀቁ ነው፤ ለበረሀ ታጋዬች ልዩ አድልኦ ስለሚደረግ መሆኑን ፖሊሶቹ አጋለጡ፤ የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን አዲስ ሹመት ደርቦ እንዲሰራ በምስጢር ተሾመ >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ.......................**

የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ምስጢራያዊ ስብሰባ በወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቢሮ ውስጥ ለሁለት ቀናት ማድረጋቸውን ከቤተ መንግስት ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ።

በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰብሳቢነት 45 የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ለሁለት ቀናት ባደረጉት ዝግ እና ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ እርስ በርስ አተካሮ እና ሙግት ውስጥ ገብተው እንደነበረ የገለፁት ምንጮቹ በዕለቱ መለስ ከመናደዱ የተነሳ እራሱን በሁለት እጆቹ ይዞ ለረዥም ደቂቃዎች አቀርቅሮ እንደነበረ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

በሀገር ውስጥ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ፤ በውጭ ሀገር በተለይም በሱማሊያ ውስጥ በደረሰበት ስር የሰደደ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ኪሳራ ምክንያት ዙሪያው ገደል የሆነበት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለስልጣናቱን ሰብስቦ እየገላመጠና እየተሳደበ የዋለ ቢሆንም ባለስልጣናቱም እንደቀድሞው ዝም ከማለት ይልቅ መልስ በመስጠት የበለጠ ናላውን እንደበጠበጡት የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ ከአፈ ጉባኤ ተሽመ ቶጋ ጋር ከፍተኛ ሙግት ውስጥ ገብተው እንደነበረም ጨምረው ገልፀዋል።

መለስ የእያንዳንዱን ባለስልጣን ስም እየጠራ ሲዘልፋቸውና ሲሰድባቸው የነበረ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በተለይ ተሽመ ቶጋን « የተሰጠህን ስራ በአግባቡ ሳትወጣ ለ5 ቀናት ለስራ ጉዳይ ብትላክ ሽርሽር ከርመህ መምጣትህ ኃላፊነትህን በአግባቡ አለመወጣትህን ከሚያመለክት በተጨማሪ እንዝህላል መሆንህን ያሳያል» ሲል አይኑን እያጉረጠረጠ ከፍ ዝቅ አድርጎ ዘለፋ እንደሰነዘረበት ምንጮቹ ገልፀዋል።

የመለስን ስድብና ዘለፋ በጥሞና ሲያዳምጥ የቆየው ተሽመ ቶጋም « ከሀገር ስወጣ የሰጣችሁኝን አበል እናንተ ታውቁታላችሁ ።ለ5 ቀናት መሆኑን አትዘነጉትም ።ነገር ግን ለሀገርና ለህዝብ ስል በገዛ ገንዘቤ ስሰራ መቆየቴ የሚያስመሰግነኝ እንጂ የሚያስወቅሰኝ አይደለም ። ስለዚህ አሁን እየተናገርክ ያለው ሁሉ የተሳሳተ በመሆኑ ቅሬታህን ልታነሳ ይገባል» በማለት ደም ስሮቹ እየተገታተሩ ምላሽ እንደሰጠው ምንጮቹ አብራርተዋል።

መለስ ከነዚሁ 45 ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ዐርብ ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም.ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሲሙዋገት ያመሸ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ በተለይ ከተሾመ ጋር እሰጥ አገባ በገባበት ወቅት ለ30 ደቂቃ ያህል አንገቱን ደፍቶ ከቆየ በሁዋላ ከአቅሙ በላይ የሆነ የራስ ህመም ስላጋጠመው « እራሴን ስላመመኝ ትንሽ አረፍ ልበል » በሚል ከስብሰባ አዳራሹ ወጥቶ የነበረ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል።

ከመለስ ጋር ስብሰባ ሲቀመጡ ለወትሮው በፍርሀትና በድንጋጤ የሚንቀጠቀጡት የወያኔ ባለስልጣናት ሰሞኑን ግን ምን እንዳገኙ ባይታወቅም ደፍረው መልስ መስጠት መጀመራቸው ምናልባትም ሰዎቹ ተስፋ ቆርጠው ሊሆን ይችላል ሲሉም ምንጮቹ አብራረውተዋል።

በተደጋጋሚ ጊዜ «አሁን ያለንበት ከመቸውም ጊዜ በላይ አጣብቂኝ ውስጥ የገባንበት ወቅት በመሆኑ እያንዳንዳችሁ የተሰጣችሁንና የሚሰጣችሁን ኃላፊነት የማስፈጸም አቅማችሁ ከቀን ወደ ቀን እየተዳከመ በመሆኑ ልታስቡበት ይገባል።» በማለት እምቡዋ ከረዩ ሲል ማምሸቱን ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል።

በዚሁ ስብሰባ ላይ እንደተገለፀው ከሆነ ሰሞኑን የተደረገው የሚኒስትሮች ሹም ሽረት የሚቀጥል መሆኑን እና በተለይም የህዝብ ግንኙነት ሰራተኞች በበቂ ሁኔታ የሰለጠኑ በመሆናቸው በቅርቡ በሁሉም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ይመደባሉ። በሁሉም መስክ እገዛ ልታደርጉላቸው ይገባል ያለው መለስ ዜናዊ በጄኔራሎቹ መሀከል ስለተከሰተው ግጭትንም በተመለከተ በጥቂቱ ጠቆም አድርጎ ማለፉን በዝርዝር አስረድተዋል።

ከህዳር 26 ቀን እስከ ህዳር 27 ቀን 2001 ዓ. ም. ድረስ በስብሰባ ተወጥረው የቆዩት የወያኔ ባለስልጣናት ባደረባቸው ስጋትና ፍርሀት ምክንያት ዙሪያቸውን ከውጭ በኩል ቀይ ቆብ በደፉ ወታደሮች በእግረኛ እና በፓትሮል ሲጠብቁ በቤተመንግስቱ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ግቢ ውስጥ ደግሞ ባለ ጎማው ብረት ለበስ ከባድ መሳሪያ ተወጥረውና ተከብበው እንደነበረ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

በስጋትና በፍርሀት ተወጥረው ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ በምስጢር እየዶለቱ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ለይምሰል ላይ ላዩን አንድ ይምሰሉ እንጂ ውስጥ ውስጡን ግን ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው የገለፁት ምንጮች የሰሞኑም መወራረፍ የሚያመለክተው ይሄንኑ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የሱማሌ ጉዳይ ናላውን የበጠበጠው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በስብሰባው ላይ የሚያደርገውና የሚያወራው ሁሉ ጠፍቶት በንዴት እየተወራጨ ጠረጴዛውን በቡጢ ደጋግሞ እየደለቀ ኮቱን አውልቆ በጉርድ ሽሚዝ ሆኖ አይኑን እያጉረጠረጠ ቢያስፈራራቸውም የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ ባለስልጣናቱም ያለ አንዳች ፍርሀት ሙግት መግጠማቸው ንዴቱ እየጨመረ መጥቶ ለ30 ደቂቃ ያህል ልዩ ክፍል ውስጥ እንደቆየ የገለፁት ምንጮቹ በወቅቱ ሁኔታው አስጊ ስለሆነባቸው ሀኪሙ ተጠርቶ እንደነበርና የማስታገሻ መድሀኒት እንዲወስድ ተደርጎ ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንደተመለሰ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

የመን ድረስ በራሱ ጥያቄ አቅራቢነት የሄደው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቀዝቃዛ አቀባበል የተደረገለት ከመሆኑም በተጨማሪ ለየመኑ ፕሬዝዳንት ላቀረባቸው ጥያቄዎች በሙሉ  አጥጋቢ ምላሽ ሳያገኝ እናስብበታለን ተብሎ በመመለሱና ከሱማሌ ውስጥም ጦሩን እንደሚያሰውጣ ቃል ገብቶ የመጣ ቢሆንም መውጣቱን እንደ ሽንፈት በመቁጠር እንደገና ሌላ ተጨማሪ  ጦር ወደ ሞቃዲሾ እና ባይደዋ ማስገባት የጀመረ ሲሆን በዚህም ምክንያት የተነሳ በጄኔራሎቹ መሀከል የተነሳው ሽኩቻ እንዳሳሰበው እና እንዳስጨነቀው ጠቆም ያደረገው መለስ አሁንም በይፋ ያላወጣው እጅግ ከአቅሙ በላይ ሽክም የሆነበት ነገር እንዳለ እየሰራ ያለው ድርጊቶች የሚያሳብቁበት ነው ሲሉም  ምንጮቹ  ጨምረው ገልፀዋል።

ከቀን ወደ ቀን ስጋትና  ፍርሀት እያየለባቸው የመጣው የወያኔ  መሪ መለስና ባለቤቱ አዜብ መስፍን መኖሪያቸው  በሆነው የላይኛው ቤተ መንግስት ዙሪያ ከ3 ቶን በላይ የሚጭኑ አነስተኛ መኪኖችን ጨምሮ ሌሎች ትላልቅ መኪኖች እንዳይንቀሳቀሱ የተከለከለ መሆኑን ምንጮቹ ገልጸው ከዚህም በተጨማሪ በግቢው ውስጥ ወትሮ ከነበረው የጥበቃ ማማ በተጨማሪ በግንብ የተገነቡ አዳዲስ የጥበቃ ማማዎች በ50 ሜትር ርቀት እንደተገነቡና ስራ እንደጀመሩ ጨምረው አስረድተዋል።

በዚሁ ውጥንቅጡ በወጣው ስብሰባ ላይ ባለስልጣናቱን ሲያነሳና ሲጥል የነበረ ቢሆንም የኦህዴድ ሊቀመንበር እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ቀድሞ በረሀ እያሉ የውሀ ጀሪካን አመላላሽ የነበረውን አባዱላ ገመዳ የተባለውን ሆድ አደር በሌለበት ደጋግሞ ያሞግሰውና ያወድሰው እንደነበረ  የገለፁት ምንጮች ይህንንም ሙገሳና ምስጋና የሰጠው ከኦነግ እራሳቸውን ያገለሉትን እነ አባቢያ አባጆቢርን እና ሌሎችንም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና የተልፈሰፈሰ አቋዋም እንዲይዙ ያደረገ በመሆኑ ነው ሲሉም ምንጮቹ አብራርተዋል።

በተለይ በቅርቡ ከ24 ዓመታት በላይ በካናዳ የቆየውን እና ነባር የኦነግ አባል እንደሆነ የሚነገርለት የኦሮሚኛ ዘፋኝ ቀመር ዩሱፍን ልቡን በጥቅምና በመለማመጥ አሸፍቶ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመጣ ያስደረገ እና ለአንድ የሙዚቃ ኮንሰርት ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የከፈለው ይኸው አባዱላ ገመዳ መሆኑን የጠቀሱት ምንጮች  ከቀን ወደ ቀን ፖለቲካው እየተበላሸበት በመምጣቱ  ስጋት የገባው መለስ ቀንደኛ ተቀናቃኝ ነው ብሎ የሚወነጅለውን ኦነግን ለማዳከም እየሰራልኝ ነው ብሎ በማሰቡ አባዱላ በሌለበት ሁሉ እያሞገሰውና እያወደሰው እንደሚገኝ ምንጮቹ በዝርዝር አብራርተዋል።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ወያኔ ከአንዱ የችግር  አረንቋዋ ሳይወጣ ሌላ እየተደቀነበት ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ እየዳከረ ባለበት በዚህ ወቅት ሰሞኑን የጅቡቲ ወደብ ታሪፍ ጭማሪ መደረጉ የበለጠ የነበረበትን የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳባባሰበት ከጉምሩክ ቢሮ የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

ከ6 ወር በፊት የጅቡቲ መንግስት የወደብ ጭማሪ ለማድረግ ጥናት አድርጎ መጨረሱን ባሳወቀበት ወቅት የታሪፍ ጭማሪው እንዳይደረግ ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት እስማኤል ጌሌህ መለማመጫ  እና እጅ መንሻ ለቤተሰቡ ጭምር መሬት በነጻ የሰጠው መሆኑን ያስታወሰው ዘገባው አዲስ አበባ ውስጥ ዘመናዊ ቪላ ህንፃ መስሪያ 500  ካሬ ሜትር ፤ ድሬዳዋ ቀድሞ ካስገነባው ሆቴል በተጨማሪ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ

የሚሆን 500 ካሬ ሜትር ፤ደብረዘይት ሆራ ሀይቅ ዙሪያ መናፈሻ ለመገንባት እንዲችል 500 ካሬ ሜትር በነፃ የተሰጠው ሲሆን ፤ በባሌ የእርሻ ኢንቨስትመንት ለመጀመር እንዲችል በባለቤቱ እና በልጁ ስም በሺህ የሚቆጠር ሄክታር ለም መሬት አሸክሞት የነበረው መለስ ልመናውና ልምምጡ ሳይሳካለት ሰሞኑን የወደቡ ታሪፍ ጭማሪ ተግባራዊ መደረጉን ተከትሎ ወያኔ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እንዲገባ እንዳስገደደው ዘገባው ገልጾዋል፡፡

ለአስመጪ እና ላኪ ነጋዴዎች እና ወያኔ እራሱ ለሚያስመጣቸው ነገሮች ማስገቢያም ሆነ መግዣ የሚሆነው የውጭ ገንዘብ የሌለው ወያኔ ይባስ ብሎ አሁን የወደብ ክፍያው መናሩ ሌላ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ መግባቱን ያመላክተ ነው ያለው የደረሰን ዘገባ በተለይ ጣራ ነክቶ የነበረው የብረትና የሲሚንቶ ዋጋ ከእንግዲህ የማይቀመስበት ደረጃ ላይ መድረሱን በሰሞኑ የተከሰተውን የዋጋ ሁኔታ የተከታተሉ ወገኖች ማስረዳታቸውን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ከውጭ የሚመጡ እቃዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ለውጥ እየታየ ሲሆን ወደብ ደርሰው ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ የተዘጋጁ እቃዎች የወደብ ኪራይ የሚከፍሉት የውጭ ምንዛሪ ስለሌላቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ከመውደቃቸውም በተጨማሪ እዳው በየቀኑ እየጨመረ ስለሚሄድ በወደቡ ባለንብረቶች ሊነጠቁ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ለብጥስጣሽ ሀገር መሪዎች ሁሉ እያጎበደደ ያለው መለስ ዜናዊ የመን በራሱ ጠያቂነት ሄዶ ያለምንም ውጤት ደርሶ በተመለሰ በሳምንቱ የጅቡቲው ወደብ ጭማሪ በመደረጉ ናላው ከመበጥበጡም በላይ የባለስልጣናቱ ሁኔታም አስፈሪ እየሆነበት እንደመጣም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ምንም አይነት የውጭ ሀገር ምንዛሪ ገንዘብ የሌለ በመሆኑ ነጋዴዎች ስራ ለማቆም እንደተገደዱ የገለፀው የደረሰን ዘገባ የጥሬ ዕቃ ማስገቢያ የውጭ ምንዛሪ ያጡ ባለፋብሪካዎች ስራ ለማቆም እየተገደዱ መሆናቸውንም ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

ከወደቡ ታሪፍ በተጨማሪ በኢትዮ- ጅቡቲ መስመር ላይ ያልታወቁ ታጣቂዎች በአካባቢው ላይ ሰፍሮ በሚገኘው የወያኔ ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት እየሰነዘሩ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱበት ከመሆኑም በላይ በሹፌሮች ላይም ግድያ እየተፈፀመ በመሆኑ እንደልብ ለመንቀሳቀስ እንደተቸገሩ ሹፌሮች በምሬት እየገለፁ መሆናቸው ታውቆዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ በመጉዋዝ ላይ በነበሩ የሎቤድ መኪና ሹፌሮች ላይ ጥቃት ተሰንዝሮ አንደኛው ሹፌር ወዲያውኑ ሲገደሉ ሌሎች መኪና አቁመው በማምለጥ ህይወታቸውን ለማትረፍ እንደቻሉም እነዚሁ የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሹፌሮች በምሬት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወንጀልን እንከላከላለን ሙስናን እንዋጋለን እያሉ ሲምሉና ሲገዘቱ የኖሩት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከፍተኛ መኮንኖች አዲስ ህንፃ ለማሰሪያ በሚል ብዙ ሚሊዮን ብር መመዝበራቸው ተጋለጠ፡፡

ከአጼ ኃይለ ስላሴ ጊዜ ጀምሮ ፖሊስ ሲጠቀምበት የኖረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ፅህፈት ቤት በቅረቡ ፈርሶ በምትኩ ሌላ አዲስ ባለ 8 ፎቅ ህንፃ ለማሰራት ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን ነባር ቢሮዎቹን አፍርሶ ፍርስራሹን ብቻ ለማውጣት በሚል ከ7 ሚሊዮ ብር በላይ እንደመዘበሩ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ባለ 8 ፎቅ ህንፃ ለመስራት ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት የተመደበለት ቢሆንም አፈር ለማስጠረጊያ ተብሎ ከዋና ኮሚሽነሩ እስከ መምሪያ ኃላፊዎች ድረስ ያሉ ባለስልጣናት 7 ሚሊዮን ብር ከኮንስትራክሽን ድርጅት ባለቤት ጋር ተመሳጥረው እንደተከፋፈሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ከዚሁ ገንዘብ ዝርፊያ ጋር ተያይዞ መኮንኖቹ እርስ በርስ ውዝግብ የፈጠሩ ሲሆን በተለይ ከፍተኛ የፖሊስ ኃላፊዎቹ ገንዘብ አንሶናል በሚል በቃላት እየተወራረፉ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ የኦህዴድ አባሉ ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ የተባለው ግለሰብ ከፍተኛውን ድርሻ በመውሰዱ ከፍተኛ መኮንኖቹ ውስጥ ውስጡን ቅሬታቸውን እየገለፁ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ወንጀልን እንከላከላለን፤ ምዝበራን እናወግዛለን እያሉ ሲለፍፉ እንዳልነበር ዛሬ በግላጭ የህዝብ ገንዘብ ዘርፈው እርስ በርስ እንደ ጆፌ አሞራ ሲጣሉ መሰንበታቸው የስርዓቱ መገለጫ ባህሪው ነው ያሉት ምንጮቹ ቀድሞ የነበረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ተስፋዬ መረሳ ከገንዘብ ቅሌት ጋር ተያይዞ ስልጣኑን ከተነጠቀና ከተባረረ ብዙ ጊዜያትን ያስቆጠረ ቢሆንም አስቀድሞ እሱ በነበረበት ወቅት ህንፃው እንዲሰራ ከግለሰቦች ጋር ብዙ ስምምነቶችን ያደረገው እሱ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ከግለሰብና ከተለያዩ ተቋማት ላይ በወሰደው ብር ዙሪያና በሌሎችም ምክንያቶች በአሁኑ ሰዓት ፀረ- ሙስና ኮሚሽን በተባለው የወያኔ ተቋም ጉዳዩ ተይዞ እየተጠና መሆኑን ጨምረው አስረድተዋል፡፡

የአዜብ መስፍን የአክስት ልጅን የሚያገባው ይኸው የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ የነበረው ተስፋዬ መረሳ ወደ አሜሪካ ጠፍቶ ሄዶ በአዜብ አማካኝነት ተመልሶ ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ የተደረገ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ከስልጣኑ ተባርሮ በቁም እስተረኛነት እያንገላወደ እንደሚገኝም ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በቅርቡ ህንፃ ይሰራል በሚል ብዙ ሚሊዮን ብር እየመዘበሩ ያሉት የወያኔ ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖች የእርስ በርስ ሽኩቻቸው እየጎላ በመምጣቱ ምናልባትም በደህንነቶች ጉዳያቸው ታይቶ ለእስር ሊዳረጉ እንደሚችልም ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡

እነዚሁ የወያኔ ከፍተኛ ፖሊሶች ሀብታም ነጋዴዎችን በሌሊት ከየቤታቸው እየለቀሙ ኦሮሞውን የኦነግ አባል ነህ ገንዘብ ስታዋጣ እንደነበር ተደርሶበታል፤ አማራውን የአርበኞች ግንባር አባልና የከተማ ውስጥ አስተባባሪ ነህ እያሉ በሀሰት እያስፈራሩና እያሰቃዩ ከፍተኛ ገንዘብ እየተቀበሉ መሆናቸውን የገለፁት ምንጮቹ ይህንን ወንጀል ደግሞ ከተራ ፖሊሶች ጋር ተመሳጥሮ ይሰራ የነበረው ተስፋዬ መረሳ እንደነበረና አሁን ከስልጣኑ ሲባረር ደግሞ ሌሎቹ የተተኩ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆነው ፍቃዱ ሰቦቃ የተባለው የኦህዴድ ካድሬም ከግለሰቦች ጋር ተመሳጥሮ ለፖሊስ ፅህፈት ቤት መሆን የማይችለውን ህንፃ በወር 120 ሺህ ብር በላይ እየከፈለ በመገኘቱ በሁለት መንገድ እየተወነጀለ መሆኑን እነዚሁ ምንጮች አጋልጠዋል።

ምንጮቹ እንዳሉት ከሆነ ይኸው የኦህዴድ ካድሬው ፍቃዱ ሰቦቃ የተባለው ኮሚሽነር በ120 ሺህ ብር በወር እንደሚከፍል ውል ይፈራረም እንጂ የሚከፍለው የህንጻ ኪራይ 70 ሺህ ብር ብቻ እንደሆነና በየውሩ 50 ሺህ ብር ለግሉ እንደሚያስቀር በመታወቁ እና ህንጻው ለፖሊስ መገልገያ ቢሮነት የማይሆን መሆኑን እያወቀ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ብቻ መከራየቱ ከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ እንደጣለው ምንጮቹ አስረድተዋል።

በተያያዘ ዜና በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ፖሊሶች ስራቸውን እየለቀቁ ወደ ትውልድ ሀገራቸው እየሄዱ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገለፀ።በአባሎች መሀከል አድልኦ መኖሩን ብዙ ጊዜ በየስብሰባውና በየግምገማው ላይ ቢገልፁም አድማጭ አጥተው የቆዩት እነዚሁ የቃሊቲ እስር ቤት ፖሊሶች ሰሞኑን ብቻ ከ25 በላይ የሚሆኑት ፖሊሶች በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን እየለቀቁ መሄዳቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

በጥቅምትና በህዳር ውስጥ ብቻ ከ25 በላይ ፖሊሶች የለቀቁ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ብዙዎቹ ስራ የለቀቁት ፖሊሶች ከኦሮሚያ እና ከደቡብ ክልል ተቀጥረው የመጡት እንደሆነም ጨምሮ አብራርቶዋል።

ከበረሀ ለመጡት የህወሀት ፖሊሶች የተለየ ከበሬታ እና ጥቅማጥቅሞች የሚሰጣቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ከ4ኛ ክፍል በላይ ያልተማሩ ሆነው ሳለ ሻለቃ እና ከዛም በላይ ማዕረግ እየተሰጣቸው እና ቁልፍ ቦታዎችን በሙሉ ይዘው ወጣት ፖሊሶችንና የተማሩትን በሙሉ ጫና እየፈጠሩባቸው በመሆኑ ፖሊሶቹ ስራቸውን ለመልቀቅ እንደተገደዱ ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

የማዕረግ እድገት ሲመጣም ከበረሀ ለመጡት የህወሀት ታጋዬች ብቻ ተነጥሎ እንደሚሰጥ የገለጸው የደረሰን ዘገባ በዚህም ምክንያት ፖሊሶቹ ተስፋ በመቁረጥ እና አዛዥ ተብለው የተቀመጡት ሰዎች የትምህርት ደረጃቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ለመግባባትና አብሮ ለመስራት እንደማይቻል እየገለፁ ወደ ትውልድ ሀገራቸው እየሄዱ መሆኑንም አስረድቶዋል።

በፖሊሶቹ መልቀቅ የተደናገጠው የቃሊቲ እስር ቤት አዛዥ የወያኔው ቀንደኛ የበረሀ ታጋይ አበበ ዘሚካኤል የእስር ቤቶቹን አለቆች እና እየለቀቁ ያሉትን ፖሊሶች ሰብስቦ ቢያወያይም ምንም መፍትሔ ሳያገኝ ያለ ውጤት መበተኑን ከስራ የለቀቁ ፖሊሶች ገልፀዋል።
ከእስረኞች ጋር ለምን ተነጋገራችሁ? የተለየ ግንኙነት ቢኖራችሁ ነው እያሉ ከደሞዛቸው ላይ እንደሚቀጡ የገለፁት እነዚሁ ከስራ የለቀቁት ፖሊሶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እውቁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮን ስታነጋግሩ ታይታችሁዋል በሚል ሀሰተኛ፣ ፈጠራ እና ሰንካላ ምክንያት ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ እንደሚቀጡ ፖሊሶቹ አጋልጠዋል።

እንደ ሌሎች እስረኞች ሁሉ በእውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ ላይ ወከባና እንግልት እንድናደርስበት ብንታዘዝም አንፈፅምም በማለታችን በእስር ቤቱ ባለስልጣናት ጥርስ ውስጥ ገብተናል ያሉት የተማሩትና ወጣት ፖሊሶቹ ለቲዲ  አክብሮትና አድናቆት በመስጠታቸው የተነሳ ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ጋር እየፈረጁ ሊወነጅሉንም ይዳዳቸዋል ሲሉ በምሬት ያሳለፉትን ስቃይ አስረድተዋል፡፡

በሌላ ዜና የወያኔው ቱባ ባለስልጣን ወዲ ሻምበል የተባለው ግለሰብ አሁን ከያዘው ከፍተኛ ስልጣን በተጨማሪ ሌላ ተደራቢ ሹመት በምስጢር ከመለስ ዜናዊ እንደተሰጠው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ምክትል ዳይሬክተር የሆነው ወዲ ሻምበል የተባለው የወያኔ ባለስልጣን ከዚህ ሹመት በተጨማሪ በተደራቢነት የደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣን ሆኖ ደርቦ እንዲሰራ በምስጢር የወያኔው  መሪ መለስ ዜናዊ እንደሾመው ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ከጥዋቱ 3 ሰዓት እስከ 8 ሰዓት ድረስ በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር  ኮሚሽን ፅህፈት ቤት እንዲሰራና ከ8 ሰዓት በሁዋላ ደግሞ እስከ ምሽቱ ድረስ ከመረጃና ደህንነት ግብረ ኃይል ጋር አብሮ እንዲሰራ መሾሙን ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

የማረሚያ ቤት ዋና ዳይሬክተር የነበረውን መኮንን አሰጌ የተባለውን ባለስልጣን ሰበብ አስባብ እየፈለገ እያበሳጨው በማስቸገሩ በህመም ምክንያት ስልጣኑን በገዛ ፈቃዱ እንዲለቅ ያስደረገ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው መኮንን አሰጌ የተባለው የያዘውን ስልጣን ለመውሰድ ሲል ብቻ ከፍተኛ ሸር እና ደባ ሲሰራበት የነበረው ይኸው ወዲ ሻምበል  የተባለው ግለሰብ እንደነበረም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በሸርና በተንኮል አለቃውን ቢያባርርም እስከ አሁን ድረስ ቦታው ያልተሰጠው ወዲ ሻምበል የተባለው የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ  ለመለስ  ካለው ቅርበት የተነሳ የደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣን ሆኖ ለመሾም እንደበቃም ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ያሉ እስር ቤቶች በእስረኛ ብዛት ተጨናንቀው የሚገኙ ሲሆን በተለይ ቃሊቲ እና ዝዋይ እስር ቤቶች በእስረኛ በመጨናነቃቸው የተነሳ ወደ ሸዋ ሮቢት እስረኞችን እያጉዋጉዋዙ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በተለይ ከቃሊቲ እስር ቤት ዘወትር ቅዳሜ ከ8 እስከ 10 አውቶቡስ እስረኞችን ይዘው ወደ ሸዋ ሮቢት እየተጉዋጉዋዙ ሲሆን እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮም ይግባኙ እስከ ዐርብ ድረስ  ካልደረሰለት  ወደ ዝዋይ አሊያም ሸዋ ሮቢት እንደሚላክ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፃ ያስረዳል፡፡